# አልነገርኩሽም ወይ !!



አልነገርኩሽም ወይ - ፍቅር ተሰርዞ፣

በየቦታው ሁሉ - ሰው ሶልዲ አርግዞ፣

ጥሎ ማለፍ ሆኖ - መተዛዘን ቀርቶ፣

አንዱ እየበላ - ሌላው ተኮራምቶ፣

ግዜ ጉድ አሳየን - ገንዘብ ሰው ተክቶ፣

ዘመን ጉድ አሳየን - ሰው ገንዝብ አርግዞ፣

ጾታ መች ለየና - ሁሉም ተቀብድዶ፣

የሰው ልጅ አምጦ - ሶልዲ ወለደና፣

ፍቅሩ ጠፋና - ገንዘብ ነገሰና፣

የሰው መዋደዱን - ገንዘብ ተካውና፣

አንዱ አንዱን ገድሎ - ለብር እየሞተ፣

ወደጁን በገንዘብ - በጠንቋይ መትቶ፣

እርህራሄ አጥቶ - ስብዕና ጠፍቶ፣

ወንድምና እህት - በብር ተክቶ፣

ሶልዲ ነው የነገሰው - የሰው ልጅ ተጠልቶ፣

ገንዘብ እምነቱ ነው - አምላኩንም ትቶ፣

አልነገርኩሽም ወይ - ፍቅር ተሰርዞ፣

በየቦታው ሆሉ - ሰው ሶልዲ አርግዞ።

መይሳው ከምድረ ስዊድን

2017-11-16